


ከዓለም ምግብ ፕሮግራም (WFP) እና ከCARE Denmark ጋር በመተባበር የተቋቋመው ኢግናይት የፈጠራ ውድድር በምስራቅ አፍሪካ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም እና የአመጋገብ ችግሮች ላይ ለመስራት የተመሰረተ በአይነቱ የመጀመሪያው ማዕከል ነው። ዋና አላማው በአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር እና በአካባቢው ማኅበረሰቦች የሚመራ ዘላቂ የምግብ አሰራርን መፍጠር ሲሆን፤ ማዕከሉ የአካባቢ ችግሮችን ለመፍታት፣ ስራ ፈጣሪነትን ለማጎልበት እና ተጽዕኖውን ለማስፋት ቁርጠኛ ነው።

ማዕከሉ ከWFP ETCO፣ Care Ethiopia እንዲሁም ከIceaddis ጋር በመተባበር በኢትዮጵያን የመጀመሪያውን የፈጠራ ፕሮግራም እያስጀመረ ይገኛል። የውድድሩ አላማ በምግብ ምርትና በአየር ንብረት ለውጥ ዙሪያ ችግሮችን መፍታት የሚችሉ ስራ ፈጣሪዎችን መለየት ነው።

### የውድድሩ ዓላማዎች

የኢግናይት የአየር ንብረት ፈጠራ ውድድር በአማራ እና አፋር ክልሎች የሚገኙ የተጋላጭ ማኅበረሰቦችን ልዩ ፍላጎት መሰረት ያደረጉ አዳዲስ አሰራሮችን እንዲዳብሩ በማበረታታት፣ መፍትሄዎችን ለማምጣት ያለመ ውድድር ነው። ይህ ውጥን የአየር ንብረት ለውጥ በምግብ ዋስትና እና በግብርና ላይ የሚያስከትለውን ተፅእኖ በመቅረፍ የአየር ንብረትን የመቋቋም አቅምን ለማሳደግ ይፈልጋል። ውድድሩ ስራ ፈጣሪዎች ሀሳባቸውን የሚያሳዩበት፣ ድጋፍ የሚያገኙበት እና ፈጠራዎቻቸውን የሚያጎሉበት መድረክ በማቅረብ፣ ከተለያዩ ዘርፎች የተውጣጡ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ለአየር ንብረት ችግሮች ውጤታማ መፍትሄዎች ላይ ለመድረስ ይሰራል።

### አትኩሮት/ትኩረት

1. ገበያ እና ፍጆታ

- የተመጣጠነ የምግብ ፍላጎትንና ሸቀጦችን የሚያነቃቁ አዳዲስ ፈጠራዎች፣
- ዘላቂ እንቅስቃሴዎች ላይ በማተኮር የተረጂዎችን (ድጋፍ የሚያስፈልገቸው አምራቾችን) ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ያለሙ መፍትሄዎች።

2. ከአየር ንብረቱ ጋር የሚስማማ ግብርና

- ለእንስሳት ምርት አያያዝ፣ ማቀነባበር እና የግብይት የፀሐይ/ዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም፣
- የግብርና ምርታማነትን እና የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም አቅምን የሚያሻሽሉ ቴክኖሎጂዎች እና ልምዶች መጠቀም፣
- በዲጂታል ላይ የተመሰረተ የበሽታ ምርመራ እና የሰነድ አያያዝ ዘዴዎችን ማዳበር፣
- በሽታን የሚቋቋሙ ዘሮችን እና ዘመናዊ የግብርና ቴክኒኮችን ማዳበር።

3. የውሃ ሃብት ፈጠራዎች

- ቀልጣፋ የውሃ አጠቃቀምን የሚያረጋግጡ አዳዲስ ፈጠራዎች፣
- በግብርና አውድ ውስጥ የውሃ እጥረትን፣ ጥራትንና ተደራሽነትን የሚፈቱ መፍትሄዎች።

የኢግናይት የአየር ንብረት ፈጠራ ውድድር በኩል በአየር ንብረት ለውጥ፣ በምግብ ዋስትና እና በኢትዮጵያ ዘላቂ ልማት መካከል ያለውን ውስብስብ ግንኙነት የሚፈቱ አዳዲስ መፍትሄዎችን ለመፍጠር እንተጋለን። ነገ የተሻለ እና የበልጽገ ፈጠራን ለማምጥት አሁኑኑ የጥረታችን አካል ይሁኑ።

ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ https://www.iceaddis.com/ignitehubet-am ን ይጎብኙ።